# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የቴክኖሎጂ ደህንነት ስጋትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁ .ጉ./2012

ኢመደኤ

ግንቦት 2012 ዓ.ም

# መግቢያ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ወደ ሃገር የሚገቡና ከሃገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች፣ የመረጃ አነፍናፊዎች እና የጥቃት ቴክኖሎጂዎች በሀገር ደህንነት ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ ከመከላከል አንጻር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የመቆጣጠር ተግባር እና ሃላፊነት በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ 808/06 አንቀጽ 6 (11) የተሰጠው በመሆኑ፣

ይህን ሃላፊነትና ተግባሩን በብቃት ለመወጣት እና የቴክኖሎጂ ቁጥጥር ደህንነት ፍተሻ አሰራር ሂደቱ ጊዜና ወጪን ቆጣቢ በሆነ እና ቅልጥፍናን ባረጋገጠ እና ተጠያቂነትን ባሰፈነ መልኩ ተፈጻሚ ማድረግ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

ገደብ የሚደረግባቸው ቴክኖሎጂዎችን መስፈርት የሚያወጡ፣ የምርመራ ፍተሻ የሚያደርጉ እንዲሁም የሚያረጋግጡና የሚያጸድቁ ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም የሚጠበቅ ስነ-ምግባር ግልጽ ለማድረግ፣

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.808/06 አንቀጽ 11 (2) መሰረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. ስያሜ

ይህ መመሪያ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የቴክኖሎጂ ደህንነት ስጋትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁ .ጀ /2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. **"ኤጀንሲ"** ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፤
2. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ነው፤

3. **“ቴክኖሎጂ”** ማንኛውም የሃርድ ዌር ወይም ሶፍትዌር ውጤት የሆነን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የመረጃ አነፍናፊ፣ የጥቃት ቴክኖሎጂን ወይም ሌሎች መሰል ቴክኖሎጂዎችን ይጨምራል፤

4. **“ገደብ የተደረገበት”** ማለት ብሄራዊ ጥቅም እና ደህንነት ስጋት እና አደጋን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ወይም እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ ገደብ የተደረገበት የቴክኖሎጂ አይነት ነው፤

5. **“ደጋፊ ሰነድ”** በአንድ መስኮት አገልግሎት ከሚጠየቅ ሰነድ ማስረጃ በተጨማሪ ቴክኖሎጂውን የሚገልጽ ማንኛውም ዝርዝር የጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ መልክ የተደራጀ መረጃ ማለት ነው፤

6. **“አንድ መስኮት አገልግሎት”** ማለት በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ ለገቢና ወጪ የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በተሟላ መልኩ በአንድ ቦታ ሁሉንም አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል ስርዓት ነው፤

7. **“የቁጥጥር ስራ”** ማለት አንድ ቴክኖሎጂ ገደብ የተደረገበት ስለመሆኑ እና አለመሆኑ በመፈተሽ፣ በመመርመር እና በማረጋገጥ ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ሂደት ነው፤

8. **“ስራ ክፍል”** ማለት በኤጀንሲው አደረጃጀት ወደ ሀገር ገቢና ከሃገር ወጪ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን አስመልክቶ የቁጥጥር ስራ እንዲያከናውን ሃላፊነትና ተግባር የተሰጠው ክፍል ነው፤

9. **“ሰራተኛ”** ማለት በስራ ክፍሉ ውስጥ ተመድቦ በየደረጃው የሚሰራ አመራር ወይም ባለሙያ ነው፤

10. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

11. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፤

12. አግባብ ያላቸው የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ትርጉም ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት አላቸው፤

13. በነጠላ ቁጥር የተገለጸው ብዙ ቁጥርንም ይጨምራል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች በብሄራዊ ጥቅም እና ደህንነት ላይ የሚያስከትሉትን ስጋት ቀድሞ መከላከል እና መቆጣጠር ነው።

## 4. የመመሪያው ወሰን

1. ይህ መመሪያ በኤጀንሲው ስራ ክፍል እና ሰራተኞች እንዲሁም ቴክኖሎጂን ወደሃገር ውስጥ በሚያስገቡ ወይም በሚያስወጡ አካላት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ይህ መመሪያ በሀገር መከላከያ፣ ፌደራል ፖሊስ እና የህዝብ ደህንነት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

# ክፍል ሁለት

# ገደብ ስለማድረግ እና ፈቃድ ስለመስጠት

## 5. ገደብ ስለማድረግ

ኤጀንሲው ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ላይ ሊደርስ የሚችልን ስጋት እና አደጋ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሲል ማንኛውም ቴክኖሎጂ ላይ ገደብ ሊያደርግ ይችላል።

## 6. ገደብ የተደረገበትን ቴክኖሎጂ ዝርዝር ይፋ ስለማድረግ፤

3. ኤጀንሲው ገደብ ያደረገባቸውን ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር በየወቅቱ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ እና በአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲሁም በስፋት የሚሰራጩ የመገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል።
4. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለህዝብ ተደራሽ የሆነን ገደብ የተደረገበት ቴክኖሎጂ ዝርዝር በየጊዜው የቴክኖሎጂን ተለዋዋጭነት እና ለውጥ መሰረት በማድረግ ያሻሽላል እንዲሁም ለህዝቡ ተደራሽ ያደርጋል።

## 7. ስለክልከላ

ማንኛውም ገደብ የተደረገበትን ቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማስወጣት የተከለከለ ነው።

8. ልዩ ሁኔታ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ገደብ የተደረገበትን ቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ገቢ ወይም ወጪ ማድረግ የሚፈልግ ሰው ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ኤጀንሲው ፈቃድ ሲሰጥ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማገናዘብ አለበት፡-

ሀ) በህዝብ ደህንነት እና ጥቅም ላይ ስጋት የማይፈጥር መሆኑ፤

ለ) ለጥናትና ምርምር ዓላማ እንደሆነ፤

ሐ) በህይወት እና በጤንነት ላይ አደጋ ያለማድረስ ሁኔታዎች፤

መ) ሌሎች ኤጀንሲው በየጊዜው ተገቢ ብሎ የሚወስናቸው መመዘኛዎች።

## ክፍል ሶስት
## ስለማመልከት እና አቀራረብ ስነ-ስርዓት

9. ማመልከቻ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 (1) መሰረት ፈቃድ ለማግኘት በቅድሚያ ለኤጀንሲው ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል።

2. በህግ ፍቃድ እንዲሰጡ ስልጣን ከተሰጣቸው ተቋማት የሚገኙ ሌሎች ፍቃዶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል።

ሀ) የሚያስገባው ወይም የሚያስወጣው ሰው ሙሉ ስምና አድራሻ፤

ለ) የቴክኖሎጂው ምንነት፣ ስሪት ሀገር፣ የቴክኖሎጂው መለያ ቁጥር፣ ሞዴል፣ የምርት ዓመት እና ቴክኒካዊ አቅሞቹ በትክክል የሚገልጽ እና አምራቹ ቴክኖሎጂውን አስመልክቶ የሚሰጠው የቴክኒክ መግለጫ፤

ሐ) ከተለመደው አገልግሎቱ ውጪ ለሌላ ዓላማ የመዋል አቅም ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ፤

መ) ተቋም እንደሆነ የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነትና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አካላት፣ እና

ሠ) ሌሎች ኤጀንሲው በየጊዜው ተገቢ የሚላቸው ደጋፊ ሰነዶች።

## 10. በመጠራጠር ስለማመልከት

1. ማንኛውም ሰው ገቢ ወይም ወጪ ሊያደርግ የፈለገው ቴክኖሎጂ ገደብ የተደረገበት ስለመሆን አለመሆኑ የተጠራጠረ እንደሆነ ጥርጣሬውን በመግለጽ ፍቃድ እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በአንቀጽ 9(2) ላይ የተመለከቱ ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 11. የማመልከቻ አቀራረብ ስርዓት

1. ማንኛውም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 እና 10 መሰረት የሚቀርብ እና ከንግድ ገቢና ወጪ ጋር የተያያዘ ማመልከቻ የአንድ መስኮት አገልግሎትን ስርዓትን ተከትሎ መቅረብ ይኖርበታል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በግለሰብም ሆነ ከንግድ ውጪ በተሰማራ ተቋም የሚቀርብ የፍቃድ ጥያቄ በቀጥታ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ወይም በአካል በመቅረብ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ በመሙላትና ደጋፊ ሰነድ በማያያዝ ማመልከት ይችላል፡፡

3. ኤጀንሲው በግለሰብም ሆነ ከንግድ ውጪ በተሰማራ ተቋም የሚቀርብ ፍቃድ በአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ አስመልክቶ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት ያመቻቻል።

## 12. ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 (1) እና (2) የሚያመለክት ማንኛውም ሰው ቴክኖሎጂውን ከመግዛቱ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ከማጓጓዙ አስቀድሞ የቅድመ ፍቃድ ማመልከቻ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 (1) እና (2) የሚያመለክት ማንኛውም ሰው በሀገር ውስጥ የጉሙሩክ ጣቢያ ቀርቦ ማመልከቻውን በቀጥታ ማቅረብ ይችላል።

## 13. ምላሽ ስለመስጠት

ኤጀንሲው፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 መሰረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በመፍቀድ ወይም በመከልከል በሶስት ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ምላሽ የሚሰጠው ማመልከቻው የተሟላ እና የሚጠየቁ ደጋፊ ሰነዶች ተሟልተው የቀረቡ እንደሆነ ብቻ ነው።

## 14. በድጋሚ ማመልከቻ ስለሚቀርብበት ሁኔታ

1. ኤጀንሲው ያልተሟላ ወይም የተጠየቁ ደጋፊ ሰነዶችን አያይዞ ያልቀረበ ማመልከቻን ውድቅ በማድረግ ተሟልቶ እንዲቀርብ ተመላሽ ማድረግ ይኖርበታል።
2. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 (2) እና (3) መሰረት ተመላሽ የተደረገ ማመልከቻ ተሟልቶ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 15 (3) የተመለከተውን የአገልግሎት ክፍያ አያይዞ በድጋሚ ሊቀርብ ይችላል።

## 15. ስለተመጣጣኝ ክፍያ

1. በኤጀንሲው እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ 808/2006 አንቀጽ 6 (15) በተደነገገው መሰረት በዚህ መመሪያ መሰረት ለሚሰጠው የቁጥጥር ስራ ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ክፍያን ያስከፍላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የአገልግሎት ክፍያ ተመን በተመለከተ አግባብ ባለው አካል በሚጸድቅ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚፈጸም የአገልግሎት ክፍያዎች ከተገቢው የክፍያ መጠን ጋር ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

## 16. አስገዳጅ ውል ስለመፈጸምና ክትትል በተመለከተ

1. ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ገቢ ወይም ወጪ የሚሆን ገደብ የተደረገበት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አስመልክቶ አስገዳጅ የውል ስምምነት እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚፈጸም ውል በየአመቱ መታደስ ይኖርበታል።
3. ኤጀንሲው ወደ ሀገር ውስጥ ገቢ የተደረጉ ገደብ የተደረገባቸው ቴክኖሎጂዎች ጋር በተያያዘ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚደረግ ውል ስምምነትን መሰረት አድርጎ በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የመስክ ሰራተኞችን በመመደብ በማንኛውም ጊዜ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ገደብ የተደረገበት ቴክኖሎጂ ወጪ ለማድረግ የሚፈልግ ሰው አስገዳጅ ውል እንዲፈጽም ከመጠየቁም በተጨማሪ እንደነገሩ ሁኔታ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎችን ኤጀንሲው በጽሁፍ ሊያሳውቀው ይችላል።

# ክፍል አራት

# ቅሬታ ስለማቅረብ እና ስርዓት

## 17. ቅሬታ አቀራረብ

1. ማንኛውም ሰው ከኤጀንሲው የአሰራር ስርዓት እና ውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ቅሬታ የሚያቀርብ ሰው የቅሬታ ቅጽ በመሙላት እና ስለጉዳዩ ዝርዝር መረጃ በመግለጽ ቅሬታውን፡-

   ሀ) በኤጀንሲው በጉሙሩክ ጣቢያዎች በሚዘጋጁ የቅሬታ ማቅረቢያ ቦታዎች ለሚመደብ ሰራተኛ በማቅረብ ምላሽ የሚገኝ ይሆናል፤

   ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 (ሀ) መሰረት በተሰጠው ምላሽ ላይ ቅሬታ ያለው አካል በጽሁፍ ዝርዝር ቅሬታውን በመግለጽ በኤጀንሲው የፋክስ ቁጥር ወይም ለዚሁ ተብሎ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይ በተዘጋጀ ቅጽ ቅሬታውን ገልጾ ማቅረብ ይችላል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 (ለ) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የክፍሉ ስራ ሀላፊ ጉዳዩን በማጣራት ከ2 ተከታታይ ስራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ለ) እና (ሐ) የስራ ክፍሉ ሃላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው በጽሁፍ በዝርዝር ቅሬታውን በመግለጽ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (17) ላይ ለዚሁ ተብሎ በኤጀንሲ ደረጃ ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ") ማቅረብ ይችላል፡፡

## 18. ስለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

1. ዋና ዳይሬክተሩ ከቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ጋር በተገናኘ የሚነሱ ቅሬታዎችን ሰምቶ ውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ 5 ዘርፉን የሚረዱ አባላት ያሉት ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
2. ኮሚቴው አንድ ሰብሳቢ እና አንድ ጸሃፊ እንዲሁም ሰብሳቢው በማይኖርበት ወቅት ተክቶ የሚሰራ አንድ ምክትል ሰብሳቢ የሚኖረው ሲሆን እነዚሁ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየሙ ይሆናል።
3. ኮሚቴው ከቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ጋር በተያያዘ በማንኛውም ሰው በስራ ክፍሉ አሰራር ላይ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 (መ) የሚቀርብ ቅሬታን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ቅሬታውን መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን በ 3 ተከታታይ ስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል።
5. በኮሚቴው ስበሰባ ላይ ሰብሳቢው እና ሁለት አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል። ኮሚቴው በጋራ የሚመራበትን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ማስፈጸሚያ ያወጣል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 19. ሙያዊ ስነ-ምግባር ስለማክበር

1. ማንኛውም የስራ ክፍሉ ሰራተኞች የቁጥጥር ስራን በከፍተኛ ሃላፊነት እና ሙያዊ ስነ-ምግባር ተላብሰው መስራት ይኖርባቸዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም ለማስገኘት ሲል የተጣለበትን ሙያዊ ግዴታ እና ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጣ ሰራተኛ ኤጀንሲው ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ አግባብ ባለው የሀገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

## 20. ስለምቹ ከባቢና አቅርቦት

ኤጀንሲው፡-

1. የቁጥጥር ስራ የሚሰሩ ሰራተኞች ተግባርና ሃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ምቹ ከባቢ በጉሙሩክ ጣቢያዎች ላይ እንዲኖር ያደርጋል።
2. ለሰራተኞች የተሟላ ስራ ቦታ ጤንነት ማስጠበቂያ የሚያስፈልጉ አስፈላጊ ቁሶችን ያሟላል።
3. አድርው ለሚሰሩ ሰራተኞቹ በየጉሙሩክ ጣቢያዎች ላይ አስፈላጊውን የምግብ እና የቀዝቃዛ (ውሀና ለስላሳ) እና የትኩስ መጠጥ አገልግሎት በኤጀንሲው ስታንዳርድ መሰረት እንዲያገኙ ያደርጋል።

## 21. ስለመመሪያው መሻሻል

ይህ መመሪያ በማንኛውም ወቅት በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሊሻሻል ይችላል።

## 22. ስለተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተር ከጸደቀበት ዛሬ ግንቦት ………. /2012 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።